# የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ እንቅስቃሴ (አገሬ-ክብሬ)

***(National Movement For Ethiopiawinet–Ageré-K'bré)***

## I. መግቢያ፤

የቀደምት ሥልጣኔ ምንጭ ከሚባሉትና ያልተቋረጠ መንግሥታዊ ሥርዓት ከነበራቸው ግንባር-ቀደም አገሮች አንዷና ከቅርብም ከሩቅም የተሰነዘሩባትን ያላባሩ የባዕዳን ወረራዎች ተቋቁማ ነፃነቷን ያቆየች ብቸኛዋ አፍሪቃዊት አገር፣ ታላላቅ የሚባሉ ሐይማኖቶችን በራሷ ባኅላዊ እሴትነት አቅፋ የምትገኝና በራሷ ፊደል የምትጠቀም ውድ አገራችን ኢትዮጵያ የቆዳ ስፋቷ በየጊዜው እንደገጠሟት ሁኔታዎች እየጠበበም እየሰፋም እስካሁን መቆየት የቻለችው በአጋጣሚ፣ በባዕዳን ፈቃድና ችሮታ ወይም ፍላጎት ሣይሆን ዜጎቿ በከፈሉት መራር፣ ከባድና ክቡር መስዋዕትነት መሆኑ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ነፃ አገር ሆና መቀጠል የቻለችው ልጆቿ ከውጭም ሆነ ከውስጥ የተሰነዘሩ ጥቃቶችን ተቋቁመው በተባበረ ትግላቸውና ባልተቋረጠ መስዋዕትነታቸው ላስከበሩት አገራዊ አንድነት ባላቸው የላቀ ቀናዒነት ነው። ይኸ ከትውልድ-ትውልድ የተላለፈ አኩሪ እሴት ፈተና ቢበዛበትም አሁንም የአገራቸው አንድነት ታፍሮና ተከብሮ እንዲቀጥል የተጠየቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ወደ-ኋላ የማይሉ ዜጎች ያሏት ኩሩ አገር ናት።

ኢትዮጵያችን በሁሉም ቋንቋ ተናጋሪዎችና እምነት ተከታይ ልጆቿ መስዋዕትነት የተገኘችና የሁሉም ዜጎቿ ድምር ውጤት የመሆኗን ያኽል ሕዝቧ እስካሁን ድረስ የሥልጣን ምንጭና ባለቤትነቱ ሙሉ-በሙሉ የተረጋገጠበት እና በሁሉም ረገድ እኩልነት የሰፈነበት ሥርዓት ባለቤት መሆን እንዳልተቻለም ግልፅ ነው። በመሆኑም ይቺ የጥንት ሥልጣኔ ማዕከል የነበረች፣ በርካታ ቋንቋዎች የሚነገሩባትና ያሸበረቁ ባኅላዊ እሴቶች ባለቤት የሆነች አገር በቁሣዊ ሥልጣኔ ወደ-ኋላ መቅረቷ ያንገበገባቸው ወገኖች ሁኔታውን ለመቀየር ብዙ መስዋዕትነትን ያስከፈለ ትግል በየፈርጁ አድርገዋል። ትግሉም አገራቸው ብልፅግናንና እድገትን እንድታገኝ፣ ዜጎቿም የሥልጣናቸው ባለቤት እንዲሆኑና ፍትኅን የሚያረጋግጥ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲጎናፀፉ፣ ያልተመጣጠኑና የተዛቡ ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶች እንዲስተካከሉና በማንኛውም መልክ ያሉ ጭቆናዎች ተወግደው በሁሉም ረገድ እኩልነት እንዲረጋገጥና የዜጎች የግለሰብና የወል መብቶች እንዲከበሩ ለማስቻል ነበር።

ለለውጥ በተደረገው በዚኽ የጋራ ትግልም ኢትዮጵያውያን እንደ አንድ አገር ዜጋ በጋራ በመቆማቸው አርሶ-አደሩን የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን ማድረግና መንግሥታዊ ለውጥም ማስገኘት መቻሉ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ያ የጋራ ትግል አርሶ አደሩን ከግለሰቦች ጭሰኝነት ቢያላቅቀውም ቅሉ የደርግ ጭሰኛ ከመሆን ሊያድነውና እውነተኛ የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን ባለማስቻሉ፣ እነሆ በአሁኑ ጊዜ ሕዝብ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ አዲስ ዙር ጭሰኝነት ተዳርጎ፣ አዲሶቹ ገዥዎች የአገሪቱን መሬት እንደግል ንብረታቸው በመቁጠር እንዳሻቸው እያደረጉና ያለ-አንዳች የተጠያቂነት መንፈስ ለባዕዳን ሣይቀር እየቸረቸሩት ይገኛል።

ኢትዮጵያ የዜጎቿ እኩልነት የሚከበሩባትና ከኋላ-ቀርነት ተላቅቃ የበለፀገችና ያደገች አገር እንድትሆን በተደረገ በዚኽ ቀጣይ የትግል ሂደት መኻል በብዙ መስዋዕትነት የተሸረበውን የትሥሥር ገመድ የገዘገዙ፣ ያሉንን መሠረታዊ የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴቶች የሸረሸሩ፣ ብሔራዊ ስሜትን የበረዙ፣ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንንና አንድነታችንን የሚፈታተኑ አዝማሚያዎችና አስተሣሰቦች በተጓዳኝ እንዲያቆጠቁጡና አልፎም ሥር እንዲሰዱ አመቺ

*ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። ከዚያ ለተሻለ ሥርዓት ከተደረገ ትግል ጋር በተጓዳኝ ያደጉና በጥሬው ተወስደው እየሰረፁ የመጡ አስተሳሰቦች ለምንገኝበት ውስብስብ ሁኔታ፣ በተለይም አገራዊ አንድነታችንንና ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ላይ ያሣደሩት ሥነ- ልቦናዊ ጫናና አሉታዊ አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም።*
*ከነዚኽ በሌጣው ከተወሰዱ አስተሣሰቦች አይሎ የወጣውና አሉታዊ ጎኑ አመዝኖ የሚገኘው ደግሞ ልዩነትን ዋና መሠረቱ፣ መነሻውና መድረሻው ያደረገው የፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ፍልሥፍና ነው ማለት ይቻላል።*

*በዚኽ ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ርዕዮት የተደራጀውና እንበለ አገራዊ ፍቅር እና ያለ አንዳች ብሔራዊ የኃላፊነትና የተጠያቂነት ስሜት ላለፉት ሃያ ዓመታት አገራዊ ሥልጣን ይዞ የሚገኘው ሕ.ወ.ሓ.ት. በጠባብ መሠረት ላይ የቆመ አገዛዙን ለማቆየትና የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ሲል የኢትዮጵያን ሕዝብ በ"ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች" ስም ከፋፍሎ በአገራችንና በሕዝቧ ላይ ያደረሰው ጠንቀ-ብዙ ቀውስ በተግባር እየታዬ ነው። በዘመነ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ዋነኛ የፖለቲካ ፍልሥፍና፣ የመደራጃና አልፎም የመንግሥታዊ አወቃቀር ዘይቤ እንዲሆን በመደረጉ የአገሪቱ ዜጎች ሥነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ ትሥሥር ሁሉ ይኽንኑ መሥመር ተከትሎ የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ተለያይተው እንዲያድጉና ኢትዮጵያዊ የጋራ ማንነት ሆን ተብሎ በጎሣ/ጎጥ ማንነት እንዲተካ እየተደረገ ነው።*

*ያም በመሆኑ የአገሪቱ ዜጎች በወልም ሆነ በግለሰብ ደረጃ **ሁሉም እኩል ተጠቃሚ ለሚሆኑበት የሥርዓት ለውጥ** የሚደረገው ትግል የ"ብሔር/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት" ለሚለው ደፈናዊ የፖለቲካ ቅኝት ተገዥ እንዲሆን ተደርጓል። ይኽ አሉታዊነቱ የጎላና ወደ-ኋላ ያዬ የፖለቲካ ፍልሥፍናና አስተሣሰብ ሙጥኝ ተብሎ የተያዘው ግን በሕወሓት/ኢሕአዴግ ብቻ ሣይሆን በሌሎች (በተለይም በፖለቲካው መስክ በተደራጁት ወገኖች) ጭምር በመሆኑ ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ለኢትዮጵያውያን ዋናና ገዢነት ያለው የፖለቲካችን ቅኝት እስከ-መሆን ደርሷል። ያ ደግሞ በአገሪቱ ላሉ እንደ ሰብዓዊ መብቶችና የዜጎች እኩልነት መከበር፣ ፍትኅና የሕግ የበላይነት መስፈን፣ ረሃብንና ኋላ-ቀርነትን ማስወገድ፣ ወዘተ ለመሣሰሉ **ሁሉንም እኩል ለሚመለከቱ መሠረታዊ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ** ችግሮች አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያላቸው መፍትኄዎች ለማስገኘትና በአጠቃላይ ከሁሉ በፊት የሕዝባችን የሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጥበት መልካም አስተዳደር እንዲመሠረት ሊሰጥ የሚገባው ቅድሚያና ትኩረት እንዲዳከም አድርጓል ማለት ይቻላል።*

*ስለሆነም በዚኽ ሕዝብን ከፋፋይና ወደ-ኋላ ያዬ አስተሣሰብና የአደረጃጀት ዘይቤ ላይ የሚታዩ አደጋዎችን መጠቆምና ስለ አገራዊ አንድነትም ሆነ ስለ ኢትዮጵያዊ ማንነት መቆም እንደ "ትምክኅተኛነት" ሲቆጠር፣ ብዙኃኑ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተሸማቅቀው ከተቻለ ከአንድነት ትግሉ ገለል እንዲሉ ቢያንስ ግን ጥያቄውን "በመስክ ላይ ያለ ሁኔታ ነው" በሚል አጉል "ይሉኝታ" እንዲቀበሉትና ለአናሣ ቡድኖች አጃቢ እንዲሆኑ ጥረት ሲደረግ እየታየ ነው። እነዚኽ ወገኖች ያልተረዱት ቁም-ነገር ግን ኢትዮጵያዊነት ምንም እንኳን ከመኻል፣ ከውስጥና ከውጭ ፈተና ቢበዛበትም ምናብ ሣይሆን አሁንም ሆነ ምንጊዜም በብዙ አሥርተ-ሚሊዮኖች ልብ ተቀርፆ የተቀመጠ፣ ጎልቶና ደምቆ የሚታይ መንፈስና "በመስክ ላይ ያለ" ሃቅ መሆኑን ነው። አንዳንድ ወገኖችም በአሁኑ ጊዜ ዋናው ትኩረትና እርብርብ እንደምንም "ሥልጣን ላይ ያለውን ማስወገድ" ብቻ ነው በሚል ነጠላ ጉዳይ ላይ በመጠመድ ከአንድነት ኃይሉ ይልቅ ለዚኽ ርዕዮት አራማጆች ቅድሚያ ሰጥተው ላይ-ታች የሚሉት የፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ፍልሥፍናን ዋና መመሪያቸውና የአደረጃጀት ዘይቤአቸው አድርገው የተነሱ ቡድኖች ካልታቀፉ የጋራው የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት*

ትግል ግቡን አይመታም ከሚል የተዛባ አስተሣሰብ በመነሣት ነው፡፡ ያ ዓይነት አካሄድ ግን ዘለቄታውን አስብበውትም ይሁን ባላሰቡት መንገድ፣ የአገዛዙን ዕድሜ የሚያራዝም፣ ይኸ ሕዝብን ከፋፋይ ሥርዓት ሥር እንዲሰድና በአገራዊ አንድነት ላይ ለሚደረግ እኩይ ዘመቻ አስተዋፅዖ አድራጊ ሊሆን እንደሚችል ሊያውቁት በተገባ ነበር፡፡

ይኸ የተዛባ አስተሣሰብ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንዲሰፍን በመደረጉም አገራዊና ሕዝባዊ ዓላማው ለነዚኽ ኃይሎች ጥገኛ እንዲሆንና የጋራ ትግሉን ብቻ ሣይሆን የአገሪቱ ዕጣ-ፈንታ ላይ ጭምር ወሣኝ እንዲሆኑ ለአናሣዎቹ የፍልሥፍናው አራማጆች የሌላቸውን ያልተመጣጠነ አቅም ፈጥሮላቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ያ ሥነ-ልቦናዊ ጫና ደግሞ ብዙኃኑ አገር-ወዳድ የአንድነት ክፍል ያለውን እምቅ ኃይል አኮስሶ እንዲያይና ተጎታች እንዲሆን አድርጓል፡፡ ከዚኽ የተዛባ አስተሣሰብ በመነሣትም ይኸ ነው የሚባል ሕዝባዊ መሠረት የሌላቸውና ብቻቸውን መቆም የማይችሉ ጠባብ ቡድኖች በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ኪሣራ ሕይዎት እንዲዘራባቸው ሲሞከር፣ የጋራው የአንድነት ትግልም በነሱ እንዲጠለፍና እንዲሽከረከር ሲደረግ ይታያል፡፡

ሕዝባችን በዚኽ ልዩነትን መሠረት ባደረገ ፖለቲካዊ ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ፍልሥፍና ሥር መውደቁና ያም የፖለቲካችን ገዢ ቅኝት እንዲሆን መደረጉ፤ በሥርዓት ለውጥ ፈላጊው ወገን ላይ ከፍተኛ ሥነ-ልቦናዊ ጫናን እንዳሣደረ፣ በመኻሉም አንድነት እንዳይኖርና ታጋዩ ሕዝባችን ለጋራ የማይለያይ ጥቅሙ በጋራ እንዳይቆም ዋና ምክንያት እንደሆነ፣ አገዛዙም የተቃጣበትን ተቃውሞ ለመከፋፈል ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረለትና በሥልጣን ላይ ለመቆየት ከፍተኛ ጠቀሜታን እንዳስገኘለት አጠያያቂ አይደለም፡፡ ይኸም ሁሉም አትራፊና ተጠቃሚ የሚሆንበት ፍትኃዊ የእኩልነት ሥርዓት ለማስገኘት በሚደረገው የአንድነትና የጋራ ትግል ላይ ከፍተኛ ብዥታን ፈጥሯል፤ ቅደም-ተከተላችንንም አዛብቷል፡፡ ያም ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ ለፍትኅ፣ ለእኩልነት፣ ለአንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚደረገው የኢትዮጵያውያን ትግል፣ እንዲሁም መሠረታዊ የሆነው ኢትዮጵያዊ ማንነት ለፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ጥያቄ ተገዢ ሆኖ ወደ-ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ እንዲልና ይኸንኑ ሕዝብ ከፋፋይ ዓላማ ላነገቡ ቡድኖች ጥገኛ እንዲሆን ተደርጓል ማለት ያስደፍራል፡፡

ይኸን የፖለቲካ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ፍልሥፍና መሠረት በማድረግም የኢትዮጵያ ታሪክና ማንነት ላይ ከፍተኛ የተቀነባበሩ ዘመቻዎች መደረጋቸው፣ አዳዲስ የፈጠራ ታሪኮች ሲቀፈቀፉና በረቀቀ መንገድ ኢትዮጵያዊ ትሥሥር እንዲሸረሸርና አገራዊ አንድነት እንዲቦረቦር ሲደረግ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

የ"ብሔር/ብሔረሰብና ሕዝቦች መብት" በሚል ተሸብልሎ የቀረበ ይኸ መርዘኛ ጎሠኛ የፖለቲካ ቅኝት በመሠረቱ በልዩነት ተቻችሎ መኖር ላይ ሣይሆን ልዩነት ላይ ያተኮረ አካሄድ በመሆኑ እኩልነትን፣ ፍትኅን፣ ሰላምንና መረጋጋትን አያስገኝም፡፡ እንደ-ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎችና ልዩ-ልዩ እምነቶችን የሚከተሉ ዜጎች ላሉበት አገር ቀርቶ በማንኛውም ሕዝብ መኻል ባሉ ሊፋቁ በማይችሉና ሊኖሩም በሚገባቸው ልዩነቶች ላይ አተኩሮ፣ አልፎም የፖለቲካ መርኁና የአስተዳደር መሠረቱ አድርጎ ውስጣዊ ሰላምንና ብልፅግናን ማስገኘት ከንቱ ምኞት ብቻ ሣይሆን በጣም አደገኛ የፖለቲካ ቀመር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይኸ ፍልሥፍና በ"እኛ-እና-እነሱ" እምነት ላይ የቆመ፣ ኅብረተሰባችንን የሚከፋፍልና አንድነትን የሚያናጋ፣ ከአጠቃላዩ ወደ ዝርዝሩ ያመላከተ፣ ከአንድነቱ ሥነ-ልቦናዊ ትሥሥር ይልቅ እንደ-ማንኛውም ስብጥር ኅብረተሰብ በእኛም ውስጥና መኻል በነበሩ፣ ባሉና በሚኖሩ መለያዎች ላይ ያነጣጠረ አስተሣሰብ በመሆኑ ውጤቱ ሁሉም አጥሩን አጥሮ "የየራሱን" አቅጣጫ እንዲከተልና ዜጎች ተለያይተው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣

ዘለቄታዊና አስተማማኝ ሰላም ያለው ኅብረተሰብን በአገር-አቀፍ ደረጃ ቀርቶ ለየ“ብሔር/ብሔረሰቡ” ማስገኘት የማያስችል ከፋፋይ የፖለቲካ ቅኝት ነው፡፡ ይኸ የፖለቲካ ቅኝት አናሣ መሠረት ላለው ገዢ ክፍል የተመቸ፣ ኢትዮጵያውያን እንደ አንዲት አገር ዜጎች የጋራ ዕድላቸውን በጋራ ትግላቸው እንዳይወስኑ ደንቃራ የሆነ፣ እየቆየም ልዩነታቸውን የሚያሰፋና ይበልጥ የሚያራርቃቸው፣ አገሪቱን ለባዕዳን ጣልቃ-ገብነት ይበልጥ ያጋለጠ ስለሚሆንም ሰላም አደፍራሽ፣ ሕዝባችንንም ወደ-ትርምስ የሚወስድና አገርንም የሚበትን አስተሣሰብ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

በዚኸ የፖለቲካ ፍልሥፍና አማካይነት በሚደረግ ትግል የዴሞክራሲም ሆነ የፍትኅ፣ የወልም ሆነ የግለሰብ መብት ጥያቄዎች የማይጨበጡ ግቦች እንደሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያውያን ከወዲኹ ከዚኸ መርዘኛ ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ፍልሥፍና (አስተሣሰብ) እና የአደረጃጀት ዘይቤ እስካልተላቀቅን ድረስ ስለ ግለሰብ መብቶችና ስለ ዴሞክራሲም ሆነ ስለ አገራችን አንድነት፣ ስለ ፍትኅም ሆነ ስለ እኩልነት ማሰብና ማለም ከንቱ ድካምና የማይጨበጥ ምኞት ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያውያን እንደ ግለሰብና በቋንቋ ምድብም ሆነ በአካባቢ ደረጃ መብቶቻቸውን ለማስከበር የሚደረገው ትግል የተሻለና አስተማማኝ ውጤት የሚኖረው፣ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች የወል ተጠቃሚ የሚሆኑት የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ሲጠበቅና የሚደረገውም ትግል በኢትዮጵያዊነት መንፈስና እምነት ላይ ሲመሠረት ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ **ዘር ማጣራትንና አጥንት ቆጠራን የግድ በሚጠይቅና በሚያስከትል የፖለቲካዊ-ጎሠኝነት እምነት ላይ በተመሠረተ አደረጃጀት** የማንም የቋንቋ ቡድን መብት ሊከበር እንደማይችል ነው፡፡ በወል መብት ስም በአንዲት አገር ውስጥ ለተወሰነው ክፍል ጥቅም ብቻ የሚደረግ የፖለቲካ እንቅስቃሴም ይሁን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የሚቀርብ ጥያቄ በአጠቃላዩ የሕዝብ ጥቅምና በብሔራዊ ማንነት ላይ የሚደረግ ዘመቻ በመሆኑም ተቀባይነት ሊያገኝ የማይችልና ጨርሶ ሊፈቀድ የማይገባው ጉዳይ ነው፡፡ **የኢትዮጵያ አንድነት ስንል የዜጎች የግለሰብም ይሁን የወል መብቶች የሚከበሩበት፣ ምንም ዓይነት አድልዖ የሌለበትና እኩልነት የሚረጋገጥበት ማለታችን እንደሆነም በሚገባ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡** እስካሁን የተደረገውም ሆነ አሁንም በአገር-ወዳድና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን በቆሙ ኢትዮጵያውያን የሚደረገው የአንድነት፣ የፍትኅና የእኩልነት ትግል ደግሞ ይኸንኑ በተግባር ለማረጋገጥ እንጂ ለተወሰኑ የአገሪቱ ዜጎች ብቻ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡

ምንም እንኳን ይኸ የጋራ ጎጂነት ያለው ሕዝብን ከፋፋይ ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት አስተሣሰብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ትግሉ በተደራጀ መልክ መካሄድ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተቀነቀነ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት በአደባባይ ዝቅ እየተደረግና እየተናቀ፣ ስለ ኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት መቆምና መናገርም የሚታፈርበት እንዲሆንና የኢትዮጵያ መፃዒ-ዕድል በሚጠፏት እጅ እንዲወድቅ የሚያደርግ መሯሯጥ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በጠላትነት ፈርጀው የሚታገሉ በታኝና ፀረ-አንድነት ኃይሎችን ከመንገድ በወጣ መልኩ የማስተናገድና የሌላቸውን አቅም የመፍጠር አደገኛ ሁኔታ በገሃድ እየታየ ያለበት፣ አልፎም በአንዳንዶች ዘንድ እነዚኸን አናሣ ቡድኖች “ላለማስኮረፍ” ሲባል በብዙ መስዋዕትነት የቆመችና የአንድነትና የነፃነት ዓርማ የሆነች አረንጓዴ-ብጫ-ቀይ ብሔራዊ ሰንደቅ-ዓላማችን በሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ሣይቀር እንዳትታይ እስከ-መከልከል የተደረሰበት እሣፋሪ ጊዜ ላይ ተደርሷል፡፡

ይኸ ረዘም ላለ ጊዜ እየሰመመ የመጣና በአሁኑ ጊዜ በአገር አንድነትና በመሠረታዊ ኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ የሚደረግ የተቀናበረ ዘመቻ የሚያስከትለውን አደጋ በሚገባ

*አጢኖና ነቅቶ አስቸኳይ ምላሽ መስጠት የማንኛውም አገር-ወዳድ ዜጋ ኃላፊነት ነው:: አገራዊ አንድነት ደግሞ ለኢትዮጵያዊ ማንነት በቆሙ ወገኖች እንጂ ብሔራዊ ማንነታችንን በማይቀበሉና አንድነታችንን ለማፍረስ በሚታገሉ ኃይሎች እውን ሊሆን አይችልም:: ፖለቲካዊ-ጎሠኝነትም ሆነ ፖለቲካዊ-ሐይማኖት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት በኅብረተሰብ ውስጥ ያሉ ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች ላይ ያተኮረ በመሆኑና የኅብረተሰብ ትሥሥር አውታሮችም ያንኑ የተከተሉ ስለሚሆን ዜጎችን በእኩል ማስተናገድ ይሳነዋል፤ የዜጎችን እኩልነትም ሆነ አስተማማኝ አገራዊ አንድነትን አያስገኝም::*

*ስለሆነም ይኸን የኢትዮጵያን አንድነትና ኢትዮጵያዊነትን በእጅጉ የተጻፈረ፣ የግለሰብን ኢትዮጵያዊ የዜግነት መብት የሚጥስ አዝማሚያ በዝምታ ማየት ስለማይቻል፣ የሁሉም የአገሪቱ ዜጎች ሰብአዊ ክብርና እኩልነት መጠበቅ፣ የሕዝባዊ (ዴሞክራሲያዊ) ሥርዓት እውን መሆንና ኢትዮጵያዊ እሴቶች መከበር የሚችሉት የአገራችን አንድነት ሲረጋገጥ በመሆኑ፣ የፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ቅኝትን የጋራችን በሆነው የኢትዮጵያዊነት እምነት ለመተካትና የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ዓርማ በኩራት ከፍ በማድረግ ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለአገራችን አንድነት ያለ-አንዳች ማወላወል ለመቆምና ለመታገል፣ እነሆ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን "<u>የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ እንቅስቃሴ (አገሬ-ክብሬ)</u>" በሚል ስያሜ ሕዝባዊ ድርጅት በመመሥረት በአገር-ውስጥም ሆነ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ለመንቀሣቀስ ወስነናል::*

## <u>II. አጠቃላይ ግንዛቤዎች:</u>

*እኛ ኢትዮጵያዊ አገር-ወዳድና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የቆምን ዜጎች፤*

- *በልዩ ልዩ ቋንቋዎች፣ እምነቶችና ባህላዊ እሴቶች ያሸበረቀች ውድ አገራችን ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጎቿ ድምር ውጤት መሆኗን፣ የወደ-ፊት ዕድሏም ወሣኝ፣ ዕጣ-ፈንታው የማይለያይና የጋራ ጥቅሞቹን በጋራ ኀልውናው ማረጋገጥ በሚችለው ሕዝቧ ብቻ እንደሆነና ሊሆንም እንደሚገባው በማመን፣*
- *የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያደርገው ትግል የሚከፍለውን መስዋዕትነት የሚመጥን ውጤት ሊያስመዘግብ የሚችለውና የሚያስገኘው ያለፈ ታሪኩ ብቻ ሣይሆን የወደ-ፊት ዕጣ-ፈንታው እንደማይለያይ ሕዝብ አንድነቱ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑንና፣ አንድነቱ ካልተረጋገጠ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት የሆኑት ሰላምም ሆነ መረጋጋት እንደማይገኝ፤ ስለሆነም የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ለሕዝባችን መብቶች መከበር፣ ለዜጎች እኩልነት መረጋገጥ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖርና ለእድገትና ብልፅግና መሠረት መሆኑን በመገንዘብ፤*
- *በአሁኑ ጊዜ ውድ አገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ ያሉ ዙሪያ-ጥምጥም ችግሮችን ከልብ በማጤን፤*
- *እነኝኸ አስከፊ፣ አሣሣቢና አደገኛ ክፍተትን የፈጠሩ ችግሮችም አገራችን እንደ አገርና ሕዝባችንም ዕጣ-ፈንታው እንደተሣሰረ የአንዲት አገር ሕዝብ በጋራ እንዳይቀጥል የሚያደርግ የጋራ ኀልውና-እጦት ላይ የሚጥሉ ሆነው በማግኘታችን፤*
- *የዚኸ የኀልውና-እጦት አደጋም ሆነ በሕዝባችን ላይ የሚደርስ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲሁም አጠቃላይ ግፍ፣ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ጠባብ መሠረት ላይ የቆመ የአገዛዝ ሥርዓቱን ለማስቀጠል ሲል በሚከተለው ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነትን መሠረቱ ያደረገ ሕዝብን ከፋፋይና ኋላ-ቀር ርዕዮት (የፖለቲካ ፍልሥፍናው) ማጠንጠኛና ዋና መመሪያው በማድረጉ እንደሆነ በመገንዘብ፤*

- በአገራችን ለውጥ እንዲመጣ ከሚታገሉ ድርጅቶች አብዛኞቹ በዚሁ መለወጥ አለበት የሚባለው አገዛዝ በተደራጀበት ሕዝብን ከፋፋይና ኋላ-ቀር ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ፍልሥፍናና የአደረጃጀት ዘይቤ የተደራጁ መሆናቸውን፣
- አልፎም ታሪካዊ መሠረት በሌለውና የሕዝባችንንም ሥነ-ልቦናዊና ቁሣዊ ትሥሥር እንዲሁም የወደፊት የጋራ ጥቅሞቹን በተፃረረ መልኩ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በጠላትነት በመፈረጅና የመገንጠል ዓላማን በማንገብ በቅርብና በሩቅ ካሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ እርዳታ እየታገዙ በታጠቀ አመፅ የአገራችንን አንድነት የሚፈታተኑ ቡድኖች ጎልተው የወጡበት አደገኛ ሁኔታ መኖሩን ታሣቢ በማድረግ፤
- በዚኽ ረገድ በአገራችን የተፈጠረውን የሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ክፍተት በመጠቀም ቀደም-ሲል እንደተደረገው ሁሉ አሁንም የአገራችንን ዕድል አንድ ትውልድ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዳግም በፀረ-አንድነት ኃይሎች የሚወሰንበት ሁኔታ እየተመቻቸ መምጣቱንና ጥቂቶችም አቅጣጫ ስተው አገራዊ አንድነትንና ኢትዮጵያዊ ማንነትን በተጋፋ መልኩ መንቀሣቀሣቸው ሕዝባችንን በተለይም ወጣቱን አቅጣጫ የሚያስትና የሚያዘናጋ ተግባር ላይ መሠማራታቸውን በሃዘኔታና በቁጭት በማየታችን፤ ይኽን ደግሞ በቸልተኝነትም ሆነ በለዘብተኝነት ማለፉ አግባብ አለመሆኑን በመገንዘብ፤
- በአጠቃላይ ሕዝባችንን ወደ-ባሰ ችግርና ትርምስ፣ አገራችንንም ወደ-መበተን የሚውሰድ ዕድሉ ከጊዜ-ወደ-ጊዜ ከፍ እያለ የመጣው አደገኛ ሁኔታ ጊዜ ሣይሰጠው መለወጥ እንዳለበት በማመን፤
- አጠቃላይ የኃይል አሠላለፉ በአገራችን ካለው ብሔራዊ አለኝታ የሚሆን ሁነኛ አገር-አቀፍ ኃይል ያለመኖሩ አደገኛ ክፍተት አኳያ ከውስጣዊ አጠቃላይ ውጥረት በተጨማሪ ልዩ-ልዩ የአክራሪነት አዝማሚያዎችን ለማስፋፋት ግፊት የሚደረግበት፣ መረጋጋትና ሰላምን አደፍራሽ ሁኔታዎች የሰፈኑበት አካባቢያዊና የተፈጥሮ ሃብትና ልዩ-ልዩ የኃይል ምንጮችን ለመቀራመትም ሆነ የፖለቲካ ጫናቸውን ለማሣደር ፍጥጫ በበዛበት ዓለም-አቀፍ ሁኔታ ውስጥ የምንገኝ መሆናችን ያላገናዘበ በመሆኑ በእጅጉ አሣሣቢና አዲስ ቅኝትና አስተማማኝ ምላሽ የሚያስፈልገው መሆኑን በማጤን፤
- አገዛዙን በመቃወም ለለውጥ የቆሙ ኃይሎች እስካሁን በሄዱበት የተናጠልም ይሁን የጋራ አደረጃጀት የድርጅት አጀንዳን ባስቀደመ አሠላለፍ አገዛዙን ለመቀየርም ይሁን አገራችንንና ሕዝባችንን መታደግ እንደማይቻል በመገንዘብ፤
- በአገራችን ትግል በተደራጀ መልክ መካሄድ ከጀመረ አንስቶ በተለይም ትምሕርት በቀሰመው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ ሲቀነቀንና ለብዙዎችም የፖለቲካ አፍ-መፍቻ የሆነው "በብሔር/ብሔረሰብ" ስም ተጠቅልሎ ሲስተናገድ የቆየው እና ላለፉት ሃያ ዓመታት ሕወሓት/ኢሕአዴግ የሥልጣን መሠረትና የአገዛዝ ዘይቤ የሆነው ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ለለውጥ የቆመው ኃይል ትኩረቱ ያልተበተነና በአንድ አቅጣጫ ያነጣጠረ አደረጃጀት እንዳይኖረው በማድረጉና የሕዝባችንን ኃይል በመከፋፈሉ ረገድ ቀላል የማይባል ሥነ-ልቦናዊ ጫና በማድረሱ፤ ለፍትኅ፣ ለዜጎች እኩልነትና ለኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት የሚደረገው ትግል ላይ በእጅጉ እንዳጠላበት፣ አልፎም የጋራውን ትግል ቀይዶ እንደያዘ እምነታችን ነው:: በቅድሚያ ይኽ የፖለቲካ-ጎሠኝነት ፍልስፍና ከፖለቲካ ቅኝታችን እንዲወጣና በአንድነት አስተሣሰብ ካልተተካ ሕዝባችንን የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ፣ ፍትኅና እኩልነት ሊረጋገጡና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን ሊሆን እንደማይችል በመረዳት፤
- ለሥርዓት ለውጥ የሚደረገው ትግል አዎንታዊ ውጤትን ማስመዝገብ የሚቻለው በምንም መልኩ ይሁን በምን ልዩነትን መሠረት ባደረገ አስተሣሰባና በዚሁም አስተሣሰብ ላይ በተመሠረተ አደረጃጀት ሣይሆን በአንድነት እምነትና መንፈስ

ሲሆን ብቻ በመሆኑ፣ ኢትዮጵያውያን በራሣችን ላይ መሠረታዊ የአስተሣሰብ ለውጥ ማድረግና በአገር-ውስጥም ሆነ ከአገር-ውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በአዲስ እምነትና መንፈስ፣ አቅጣጫና ትልም እንዲሰለፉ፤ አገር-አቀፍ አደረጃጀትና አወቃቀር እንዲኖራቸውና ለሕዝባችን ሁነኛና አስተማማኝ ብሔራዊ አማራጭ እንዲሆኑ የተቻለንን ማድረግ እንዳለብን አበክረን በማመን፤

- ያ እምነትና መንፈስም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መሆኑን፣ ኢትጵያዊነትና አገራዊ አንድነት ለጋራ ኅልውና መሠረት፣ ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋስትና መሆኑን በኩራትና በቁርጠኝነት በመቀበል፣
- በዚኽ በአገር ውስጥም ሆነ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያዊ የማንነት እሴቶችና ለአገራቸው አንድነት እንዲቆሙ በተመሠረተ <u>የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ እንቅስቃሴ (አገሬ-ክብሬ)</u>" ሥር የተሰባሰበን አገር-ወዳድ ወገኖች ከዚኽ በታች በተጠቀሰው ዓላማና በቀረበው አጭር የተግባር ዝርዝር መሠረት በተልዕኮው ላይ ለመሠማራት ዝግጁነታችንና ቁርጠኝነታችን ስንገልፅ በታላቅ የኢትዮጵያዊነት ክብርና ስሜት ነው::

## <u>II. ዓላማ፡</u>

የዚኽ እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ በአገራችን አዎንታዊ ለውጥ ለማስገኘት የሚደረገው ሕዝባዊ ትግል የፖለቲካ ቅኝት፣ አደረጃጀትና አሠላለፍ መነሻውና መድረሻው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ፣ ኢትዮጵያዊ ማንነትና አገራዊ አንድነት ላይ የሚደረገውን የረቀቀ ዘመቻ ለማስቆም፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ክብርና ኩራት መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና ከምንምና ከማንም በላይ ለኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት፣ ለሕዝብ ሉዓላዊት፣ ለሰብዓዊ ክብር፣ ለጋራ ኅልውናችንና ለኢትዮጵያዊ መሠረታዊ ማንነት በፅናት ለመቆምና ለመታገል ነው::

## <u>III. ተግባር፡</u>

የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ እንቅስቃሴ (አገሬ-ክብሬ) የሚከተሉት ተግባሮች ይኖሩታል::

ሀ) ይኸን የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ እንቅስቃሴ (አገሬ-ክብሬ) ዓላማ በልዩ ልዩ መንገድ ኢትዮጵያዊያን ባሉበት ሁሉ ማስፋፋትና ከእንግዲኽ ኢትዮጵያዊነትና አገራዊ አንድነት የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ቅኝትና መርኅ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፤

ለዚኽም:-

1. በዓለም-አቀፍ ደረጃ ኮሚቴዎችን በማቋቋም፣
2. ሆን-ተብሎ የተዘመተበትን ታሪካችንንና ብሔራዊ ስሜትን ለማደስ፣ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በመጥራት በታሪክ ምሑራንና በፖለቲካ አዋቂዎች፣ በአገር ሽማግሌዎችና በባለ-ሙያዎች አማካይነት ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ገለፃና ውይይት እንዲካሄድ በማድረግ፣
3. ፅሑፎችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት፣
4. የራዲዮ፣ የቴለቪዥንና የፓልቶክ ስርጭቶችን በማቋቋም፣

ለ) የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ይኸንኑ ዓላማ ተቀብለው በጋራ እንዲሰለፉ ማድረግ፤
ሐ) የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ-ድርጅት እንቅስቃሴዎቻቸውን እንዲያስተባብሩና

በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መንፈስ የጋራ አካል እንዲያቋቁሙ የሚቻለውን ጫና ማድረግ፤

ለዚኽም፤

*አንደኛ፡-* በየድርጅቱ ከድርጅታቸው አጥር ውጭ የሚያዩ አባላትን በዚኽ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሣተፉ ማድረግና እነሱም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው ድርጅታቸው በዚሁ መሥመር እንዲሰለፉ ማበረታታት፣

*ሁለተኛ፡-* ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር የጋራ ኮሚቴ በማቋቋም የፖለቲካ ድርጅቶች ስብሰባ እንዲጠሩና በዚኽ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መርኅ መሠረት ብሔራዊ አካል አቋቁመው ሕዝባዊ ትግሉ ለአገራዊ አንድነት ቅድሚያ በሰጠ መልክ እንዲካሄድ ማድረግ፣

*ሦስተኛ፡-* የአገራችንን ችግሮች ለመፍታት በዚኽ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ዓላማና መንፈስ መሠለፍ የማይፈልጉም ሆነ በተለመደው ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት ፍልሥፍናና የአደረጃጀት ዘይቤ መቀጠል የሚፈልጉ፣ አሠላለፋቸውንም ከነዚኹ ኃይሎች ጋር ማድረግ የሚመርጡ ወገኖች በአገርና በሕዝብ ላይ ከሕወሓት የተለየ አቋም እንደሌላቸው እንዲያውቁት ማስገንዘብ፣ በአገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶችም ጉዳዩን እንዲረዱትና አጠቃላይ የኃይል አሠላለፉ ይኽንኑ የተመረኮዘ እንዲሆን የተቻለውን ጥረት ማድረግ፤ ይኽንን መንፈስ ተከትለው በጋራ ለቆሙ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ መስጠት፤
ያስፈልጋል፡፡

አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ!
አንድነት ኃይል ነው፤ ኢትዮጵያዊነትም ክብር ነው!!